የተሰጠ መግለጫ

ሰኔ 22 ቀን 2010ዓም

# የወያኔ የትምህርት ፖሊሲና ውድቀቱ

የትምህርት የመጨረሻው ግብ የአንድን አገር ሕዝብ ኑሮ ሊያሻሽል የሚችል እውቀትና ችሎታ ተማሪዎች ቀስመው ያንን ወደ ሳይንስና ቴክኖሎጂ በመለወጥ የአገሪቱ እድገትና ስልጣኔ እንዲፋጠን ማድረግ ነው።በአገራችን በኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት መሰጠት ከተጀመረበት ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ኢጋማሽ ጀምሮ ትምህርት ለአገሪቱ ልጆች በጥራትና በእኩልነት እንዳይሰጥ ብዙ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ በከፍተኛ የዕድገትና ስልጣኔ ደረጃ ላይ ልትገኝ አልቻለችም። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በተባበሩት መግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባሕል ድርጅት, (United Nations Education , Scientific and Cultural organization) ፣ የአሜሪካ መንግስት ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (United States Agency for International Development) እና የዓለም ባንክ (World Bank) ገነው ወጥተው እነዚህን ድርጅቶች በመጠቀም ምዕራባውያን በሌሎች አገሮች በሁሉም መስክ ኢኮኖሚውን፣ ፖለቲካውንና ማህበራዊ ዘርፉን ለመቆጣጠር በወሰኑት መሰረት በተባበሩት መንግስታት ጽ/ቤት ስር የተቋቋመው ድርጅት የትምህርት ፣ የሳይንስና የባሕል ድርጅት አማካይነት በ1961ዓም በአዲስ አበባ ከተማ ከሁሉም የአፍሪካ አገሮች የተወከሉ የትምህርት ባለሙያዎች የሚገኙበት ስብሰባ ተካሄዶ አጠቃላይ ትምህርት ( Universal Education) ከ1ኛ-4ኛ ክፍል እንዲሰጥ ተደርጎ ፖሮግራሙ በ1972ዓም እንዲጠናቀቅ አስወሰኑ። በዚህ ውሳኔ መሰረት የዓለም ባንክ በኢትዮጵያ አጠቃላይ ትምህርት መሰጠት አለበት ብሎ በመወሰን ከ1963/64ዓም 82 የትምህርት ባላሙያዎችን( 51 ኢትዮጵያውያንና 31 የውጭ ዜጎች) የተሳተፉበት የትምህርት ዘርፍ ክለሳ ( Educational Sector Review, ESR) እንዲዘጋጅ ተደረገ። ይህ ሴክተር ሪቪው ተብሎ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታወቀው የትምህርት ክለሳ ትምህርት በስምንተኛ ክፍል እንዲቆም የሚያደርግ፣ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ቁጥር እንዲቀንስና፣ እንዲሁም አጠቃላይ ትምህርት ከ1-4ኛ እንዲሰጥ የሚያደርግ ፕሮግራም ነበር።

በዚህ ወቅት ነበር ትምህርት በጥራት ለሕዝብ ልጆች እንዲሰጥ እንዲሁም የመምህራን የመነሻ ደመወዝ እስኬል፣ እርከን ጭማሪ፣ ፍትሐዊ በመምህራን ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የዝውውር ስርዓት እንዲሰፍን፣ የትምህርት ክለሳ ፖርግራሙ ወይም ሴክተር ሪቪው የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያላስገባ፤ መምህራን፣ወላጆች፣ ተማሪዎች ያልተሳተፉበትና አስተያየት ያልሰጡበት፣ የክለሳ ፖሮግራሙ ከስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የሙከራ ጊዜ ተሰጥቶ ሊያስከትል የሚችለው ጠንከራና ደካማ ጎኖች ሳይታዩ በተግባር ላይ እንዲውል የተዘጋጀ በመሆኑ፤ ለአዲስ ተቀጣሪ መምህራን የተወሰነው 153 ብር መነሻ ደመወዝ እስኬል በቂ አለመሆኑን በመግለጽ፣ ጥናቱ በአዲሰ አበባ በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሚያስተምሩ መምህራን ላይ የደመወዝ ቅነሳ የሚያስከትል በመሆኑና ትምህርት በስምንተኛ ክፍል ተገድቦ እንዲቆም የሚያደርግ መሆኑን በመግለጽ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢመማ) አጥብቆ ተቃወመ። በተጨማሪ "ትምህርት ለሁሉም ይሰጥ"፣ " ድህነት ወንጀል አይደለም" የሚሉ መፈክሮችን በማንሳት ታግሏል። በመስከረም ወር 1966ዓም በአርባምንጭ ከተማ በተደረገው የኢመማ ጉባኤ ላይ የሴክተር ሪቪው ጉዳይ አጀንዳ ሆኖ ቀርቦ ተሰብሳቢዎቹ በጉዳዩ ላይ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና ከኮተቤ መምህራን ኮሌጅ በሁለት መምህራን ተጠንቶ የቀረበውን ጥናት አድምጠው ከተወያዩ በኋላ ሲክተር ሪቪው ተግባራዊ እንዳይሆን ወሰኑ። ለዚህና ለሌሎች የመምህራን ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥ የጊዜ ገደብ ወስኖ ለኃይለስላሴ መንግስት አቀረበ።

*ለጥያቄዎቹ መልስ የማይሰጥ ከሆነ መምህራንን የስራ ማቆም አድማ እንደሚጠራ ለመንግስት አሳወቀ። በስርዓቱ በኩል መልስ ባለመሰጠቱ የካቲት 11 ቀን 1966ዓም በአገሪቱ በሙሉ ሴክተር ሪቪውን በመቃወም፣ የመምህራን የደመወዝ ስኬል እንዲጨመር ፣ ትምህርት ለሁሉም እንዲሰጥ በመጠየቅ፣ ድህነት ወንጀል አይደለም በማለት፣ አገር አንቀጥቅጥ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ ለአንድ ወር የስራ ማቆም አድማ ተመታ። ለትምህርት ጥራትና ለመምህራን የኑሮ መሻሻል ትኩረት በመሰጠት የተጀመረው የመምህራን ትግል ህዝብ ውስጥ ሰርጾ ከሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች ማለትም የታክሲ ነጂዎች፣ የተማሪዎች፣ የሰራተኞች፣ የወታደሮች፣ የዕምነት ተቋማት፣ የሴቶች -ወዘተ ጥያቄዎች ጋር በመታገዝ የአጼው ስርዓት እንዲወገድ በማድረጉ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።*

*ደርግ የተባለው የወታደሮች ቡድን ሰኔ 21 ቀን 1966ዓም ተመስርቶ የሕዝቡን ትግል ለመቀማት እንቅስቃሴ እያደረገ በነበረበት ወቅት ኢመማ በጳጉሜ ወር 1967ዓም በጂማ ከተማ የማህበሩን አጠቃላይ ጉባኤ ጠርቶ መምህራንን፣ ተማሪዎችን፣ ወላጆችንና የትምህርት ባለድርሻዎችን ያላካተተውን በደርግ የተቋቋመውን የስርዓተ ትምህርት ኮሚቴንና የትምህርት ዝግጅትን ተቃወመ። ከሕዝብ ጎን በመቆምም "ዲምክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ "፣ "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት እንዲቋቋም" --ወዘተ በመጠየቅ ለጥያቄዎቹ መልስ የማይሰጥ ከሆነ ሕዳር ወር 1968ዓም የስራ ማቆም አድማ እንደሚያደርግ ወሰነ። ደርግ ከማህበሩ ለቀረበው ጥያቄ መልስ በመስጠት ፈንታ ከጥቅምት ወር 1968ዓም ጀምሮ የኢመማን አመራርና አባላቱን ገደለ ፣አሰረ፣ ከአገር እንዲሰደዱ አደረገ፣ የማህበሩን ገንዘብ ዘረፈ፣ ጽ/ቤቱንም ዘጋ ። ከ1971ዓም ጀምሮ ደርግ ኢመማን እንደ አንድ የፖለቲካ ክንፍ አድርጎ በመመስረት መጠቀሚያው አደረገ። ኢመማና መምህራን ለትምህርት ጥራት ያደረጉት ጥያቄ ተግባር ላይ ሳይውል ደርግ ወድቆ ወያኔ ስልጣን ያዘ።*

*እንደ ሴክተር ሪቪው በመዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራም ስም የዓለም ባንክና የዓለም አቀፍ ገንዘብ አበዳሪ ድርጅት አጋዥነት "አዲሱ የትምህርት ስልጠና" በሚል ስም ጎሳን መሰረት አድርጎ የተነደፈው ትውልድ ገዳይ የትምህርት ፖሊሲ በ1986ዓም ተግባር ላይ እንዲውል ተደረገ። ፖሊሲው አገር በቀል ማለትም መምህራንን፣ ተማሪዎችን ፣ ወላጆችንና የትምህርት ባለድርሻዎችን ሳያካትት የባዕዳንን ጥቅም ለማስጠበቅ የተዘጋጀ ነው። የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢመማ) ገና ከመነሻው ይህን የትምህርት ፖሊሲ ትውልድ ገዳይና የትምህርቱን ስርዓት አዘቅት ውስጥ እንደሚከት በመረዳት ተግባራዊ እንዳይሆን ለኢትዮጵያ ሕዝብ አሳውቋል። ለዚህም በጽናት በመቆሙና በመታገሉ አባላቱ ተገድለዋል፣ ታስረዋል፣ ከስራ ተፈናቅለዋል፣ ለስደትም ተዳርገዋል። የወያኔ አገዛዝ ደርግ እንዳደረገው ሁሉ የማህበሩን 12 ሚሊዮን ብር ዘርፏል፤ ማህበሩን በተላጣፊው ቁጥጥር ስር እንዲውል አድርጓል።*

*በዓለም አቀፍ ደረጃ በጥቅሉ የትምህርት ጥራት ሲባል ጤናቸው የተጠበቀ ፣ ከልጅነት እድሜያቸው ጀምሮ በእድገታቸው ላይ አስፈላጊ ክትትል የተደረገበት፣ የቤተሰብ፣ የትምህርት ቤትና የመምህራን ድጋፍ ያልተለያቸው ተማሪዎች ማፍራትን፤ ለትምህርት አስፈላጊ የሆኑ እቃዎች ማለትም ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ የመማሪያና የላቦራቶሪ ክፍሎች፣ መሳሪዎቻቸውና ቤተመጻሕፍት--ወዘተ ማሟላትን ፤ በትምህርት ባለሙያዎች ማለትም በመምህራን ፣ በተማሪዎች፣ በወላጆችና በትምህርት ባለድርሻዎች የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት፣ መጻሕፍት፣ ካርኩለምና የትምህርት ዝግጅት መኖርን ፤ ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ የሙያው ብቃት ያላቸው ፣ የሙያ ስልጠና የሚያገኙ ፣ በትምህርቱ ላይ ሙያዊ አስተያየት የሚሰጡ፣ምርምርና ጥናት የሚያደርጉ መምህራን፣ ለስራና ለአካዳሚክ ነጻነት አመቺ ሁኔታ ለመምህራን በመፍጠር ትምህርትን ለተማሪዎች ማቅረብን፤ አስፈለጊውን ምዘና አልፈው ለሕዝብ-ለአገር እድገትና ስልጣኔ የተማሩትን እውቀትና ችሎታ በስራ ላይ ሊያውሉ የሚችሉ ምሁራንን ማፍራትን ያጠቃልላል።*

*ወያኔ ለ27 ዓመታት ሲፈጽመው የቆየው ከላይ ከተቀጠሱት ለትምህርት ጥራት ወሳኝ ከሆኑ ተግባራት በተቃራኒው ነው። በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ የወያኔ አገዛዝ በትምህርቱ ዘርፍ የፈጸመውን ዘረፈ ብዙ ወንጀል በተለያዩ ወቅት ለመምህራን፣ ለተማሪዎችና ለወላጆች እንዲሁም ለሕዝብ ሲገልጽ ቆይቷል። ለመጥቀስ ያህል በኢትዮጵያ የትምህርት ጥራት እንዲወድቅ ለማድረግ የወያኔ አገዛዝ ለመምህርነትና ለትምህርት አስተዳደር ስልጠና ካድሬዎችን መመልመሉን፣ የከፍተኛ ትምህርት እድል የሚያገኙት በብቃት ሳይሆን ለወያኔና ለተላጣፊ ድርጅቶች ታማኝ የሆኑ ካድሬዎች መሆናቸውን፤ መምህራን የሙያ ግዴታቸውን በብቃት እንዳይወጡ ለማድረግ ግድያ፣ እስራት፣ መሰደድ፣ ከስራ ማፈናቀልና የአካዳሚክ ነፃነት ያጡ መሆናቸውን፤ የትምህርት ፖሊሲው እንዲሁም የመማሪያ መጻህፍት በባለሙያዎች የተዘጋጁ አለመሆናቸውንና ለተማሪዎች ትምህርት ሲሰጥ የቆየው የሙያ ስልጠና ባልወሰዱ የ10ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ማላፍ ባልቻሉ ወጣቶች (በአማራ ክልል) የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ትምህርት የተሰጡ መሆናቸውን ፤ የእድሜ ክልላቸው ግምገማ ለማካሄድ በማይችሉበት ደረጃ ያሉ የአንደኛ፣ የመከከለኛና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች መምህራንን እንዲገመገሙ መደረጋቸውን፤ለተማሪው ትምህርት የሚሰጥበት አካባቢ ማለትም የመማሪያ ክፍሎች፣ የመማሪያ መፃፍት፣ የላቦራቶሪ ክፍሎችና ኪሚካሎች---ወዘተ አመቺ ያልሆኑ መሆናቸውን በመዘርዘር ማቅረባችን ይታወቃል።*

*በዚህ መግለጫ ወያኔ "የሙያ ፈቃድ ምዘና " በሚል በትምህርቱ ላይ እየፈጸመ ባለው ጥቃት ላይ በጥቂቱ እናተኩራለን።ምዘና ዓላማ አለው ፤ የእውቀትና የችሎታ መለኪያ ነው። ግቡም ከፈተናው በተገኘው ውጤት መሰረት ባንድ የስራ ቦታ ወይም የዕድገት ደረጃ ላይ ለመመደብና ለትምህርቱ ጥራት አስተዋጽዖ እንዲያደርግ ነው። በወያኔው የትምህርት ሚኒስቴር በኩል በመስከረም ወር 2007ዓም የመጀመሪያው የሙያ ፈቃድ ምዘናን በሚመለከት  በት/ርት ሚኒስቴር ፌስ ቡክ ገጽ ላይ በተገለጸው መረጃ መሰረት  251,000 መምህራንና የት/ቤት አመራሮች የተመዘኑ መሆናቸውን ከነዚህም ውስጥ 38,000 የሚሆኑ ነባር መምህራንና የትምህርት ቤ/ቶች አመራሮች ወደ ማህደረ ተግባር የተሻገሩ  መሆናቸውን ይገልጻል። ምዘናውን አለፉ የተባሉት 38,000 ከአጠቃላይ ምዘናውን ከተፈተኑት 251,000 ሲቀነስ 213,000 ወድቀዋል ( 251,000 – 38,000=213,000) የወደቁት በፐርሰንት ሲሰላ 84.86% ሲሆኑ ያላፉት ደግሞ በፐርሰንት 15.14 % ናቸው። ለወደቁት መምህራንና የት/ቤት አመራሮች ምንም ተጨማሪ ስልጠና ሳይሰጣቸው በማስተማርና በት/ቤቶች አመራርነት እንዲቀጥሉ ተደርገዋል። ታዲያ የምዘና ጥቅሙ ምኑ ላይ ነው? ገንዘብንና የትምህርት ክፍለ ጊዜያትን ከማባከን ውጪ!! እነሆ ከግንቦት 11 ቀን 2010ዓም ጀምሮ ከ90,000 የሚበልጡ መምህራንና የት/ቤቶች አመራሮች "የሙያ ፈቃድ ምዘና " እንደሚወስዱ ተገልጿል። ምዘናው የመሰናዶ መምህራንን ያላካተተ መሆኑን በተለይ በአማራው ክልል ማወቅ ተችሏል። ፈተናው እንደ 2007 ዓም ግልፅነት የሌለው፤  በስህተቶች የተሞላ መሆኑን ምዘናውን ከወሰዱ መምህራን ማወቅ ተችሏል።  ወያኔ የሙያ ፈቃድ ምዘና በመስጠት ላይ የሚገኘው በአገራችን ውስጥ ሕዝቡ ከግፍ አገዛዝ ነጻ ለመውጣት ሲያደረጋቸው በነበሩት ሕዝባዊ ንቅናቄ ውስጥ መምህራን እንዳይሳተፉ ለማድረግና አቅጣጫ ለማስለወጥ ነው እንጂ ለትምህርት ጥራት አስቦ አይደለም።*

*በሌሎች አገሮች በተለይም በአሜሪካ መምህራን በተማሩበት የትምህርት መስክ ተከታታይ የሙያ ስልጠና ይሰጣቸዋል። የማስተማር ፈቃድ (Teaching Licsense) ብዙውን ጊዜ እንግሊኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ላልሆናቸው በማስተማር ሙያ ላይ ለተሳማሩ  መምህራን እንግሊዝኛ መጻፍና ማንበብ፣ ሂሳብ፣ የመማር-ማስተማር መርሆችና(Priciples of Learning and Teaching) በሚያስተምሩበት ትምህርት ዘርፍ እውቀት (Teaching Subject Content Knowledge ) ላይ ፈተናዎች ይሰጣሉ። ፈተናውን ለሚፈተኑ መምህራን ጊዜ ተሰጥቶ፣ ፈተናውን የሚወስዱበትን ቀን ራሳቸው መምህራን መርጠው ፣ለሁሉም ፈተናዎች ለጥናት የሚያስፈልጉ እቃዎች በቤተመፃሕፍት፣ በድረገጾች፣ ፈተናውን በሚሰጡ መስሪያ ቤቶችና በየትምህርት ማዕከላቱ ቀርበውላቸውና ለፈተናው ከተመደበው ጊዜ ላይ ግማሽ (1/2) ሰዓት ተጨምሮ ነው የምዘና ፈተና የሚወስዱት።በተከታታይ ተፈትነው ምዘናውን ያላለፉት  በመምህርነት ሙያ ላይ አይመደቡም። በኢትዮጵያ ግን ይህ ሁኔታ ባልተሞላበት ሁኔታ ነው ፈተናው እየተሰጠ ያለው።*

*እነሆ ከ27 ዓመታት በኋላ የወያኔ የትምህርት ፖሊሲ ትውልዱን እንደገደለ፤ የትምህርቱም ጥራት ከምንም ጊዜውም በላይ ቁልቁል እንደወረደ አገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ያፈጠጠ ሐቅ መሆኑን የአገዛዙ መሪዎች ጭምር በተለያዩ ጊዜያት ውድቀቱን ማመናቸው  ይታወቃል።  ለትምህርቱ ውድቀት፣ የመምህራን መብት ሲጣስ ዝምታ የመረጠውንና የስርዓቱ ካድሬ ሆኖ ያገለገለውን ተላጣፊ ማህበር በማፍረስ መምህራን የራሳቸውን ኢመማ ደግም መልሶ ማቋቋም የቅድሚያ ተግባራቸው ሊሆን ይገባል።ለመምህራን መብት መከበር፣ ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም የአገሪቱ ልጆች በዕኩልነት እንዲሰጥ፣በአጠቃላይ ለዲምክራሲያዊ ስርዓት እውን መሆን ብቸኛ ዋስትና ሁሉን አቀፍ የሽግግር መንግስት መመስረት ስለሆነ ለዚሁ ተግባራዊነት መምህራን ትግላቸውን ከምልዓተ ሕዝቡ ጋር እንዲያስተሳስሩ በሰደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ ይጠይቃል።*

*ለትምህርት ውድቀት ምክንያት የወያኔ የትምህርት ፖሊሲ ነው!!*
*ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም በእኩልነት እንዲሰጥ ትግሉ ይቀጥል!!*
*የትምህርት ባለቤት የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው!!*